CAMBRIDGE PUBLIC SCHOOLS (CAMBRIDGE ሕዝብ ትምህርትቤቶች)

159 THORNDIKE STREET CAMBRIDGE, MASSACHUSETTS 02141

ሜይ 23 ቀን፣ 2018 ዓ.ም

ውድ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች፣

የእያንዳንዱ ተማሪ ማህበራዊ ስሜታዊ በጎነት ለእኛ አስፈላጊ ነው። በ CPS ውስጥ ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ተመክሮ በተሻለ መልኩ መረዳት እንድንችል፣ **በጁን ወር ላይ ከ6-8 ክፍል የሆኑ ተማሪዎች ላይ የማህበራዊ ስሜታዊ የመማር እና የትምህርት ቤት ድባብ ላይ በተመለከተ መጠይቅ አዘጋጅተናል።**

በትምህርት ቤት ክፈለ ጊዜ ላይ፣ ተማሪዎች መጠይቁን መሙላት ይችላሉ። ሁለት ዓይነት ጥያቄዎች ይጠየቃሉ።

- **የማህበረሰባዊ ስሜታዊ መማር** ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ፣ ስለራሳቸው ባህሪ ምን እንደሚያስቡ፣ ስሜታቸውን መግለጽ ላይ እና ከእኩዮቻቸው ጋር ምን እንደሚሰማቸው ጥያቄዎች ይቀርብላቸዋል።
- **የትምህርት ቤት ድባብ** ተማሪዎች ስለትምህርት ቤታቸው፣ አስተማሪዎቻቸው፣ እና ጠቅላላው የትምህርት ከባቢ ላይ ምን እንደሚሰማቸው ይጠየቃሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚረዳቸው እንደሚያገኙ፣ እንደሚግባቡ እና እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ይጠይቃሉ።

ይሄ መጠይቅ የተዘጋጀው በአጋራችን፣ ፓናሮማ ኢዱኬሽን ነው። የተማሪዎች ምላሽ ሙሉ ለሙሉ በሚስጥር ይያዛል። ተማሪዎች የመጠይቁ የመጀመሪያ ስክሪን ላይ ስማቸውን ሊመለከቱ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለትምህርት ቤቱ እነሱን የሚለይ መረጃ አይላክም። ፓናሮማ ከተለያዩ የዴሞግራፊ ቡድኖች የተውጣጡ መልሶች ላይ ያሉትን ልዩነቶች ብቻ በውሂብ እና በመረጃ በማወቀር ያቀርባል።

በዲስትሪክት ዕቅዳችን አካል መሰረት ተማሪዎችን በየዓመቱ ለመጠየቅ አቅደናል፣ ይሄ የወደፊት ስኬታቸውን የሚገነባ ከግል ድጋፍ ጋር የተሟላ፣ አስደሳች፣ እና ባህል ግምት የሚሰጥ ትምህርት ለመስጠት ያለንን ቁርጠኝነታችንን ያግዛል። የእርስዎ ተማሪ ተሳትፎ ተግባራችንን ለማሻሻል በተከታታይ ለማደግ ጠቅላላ ሁኔታዎች ላይ እንድንማር ያግዘናል።

ስለዚህ መጠይቅ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ያሎት እንደሆነ፣ እባክዎ ጄኔፈር ኢሚጎን (Jennifer Amigone)፣ ዳይሬክተር ኦፍ ሪሰርች፣ አሰስመንት ኤንድ ኢቫሉዌሽን ቢሮ በዚህ ያግኙ jamigone@cpsd.us። ***ልጅዎ እንዳይሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ/የበላይን አር ብ ጁን 8 ቀን ያግኙ።***

ከእኛ ጋር ስላልዎት ቀጣይ አጋርነት እናመሰግናለን። ለወደፊቱ ስለእርስዎ እና ስለልጅዎ የበለጠ ለመማር እንፈልጋለን።

ከአክብሮት ጋር

ኬኔዝ ኤን.ሳሊም፣ ኢዲ ዲ (Kenneth N. Salim, Ed.D)
የትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ

*Cambridge ትምህርት ቤት መምሪያ እኩል ዕድል የሚሰጥ አዎንታዊ እርምጃ የሚወስድ ቀጣሪ ድርጅት ነው።*